# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)


ነሐሴ 26/2001

## 34 ዓመት የይፋ ትግል

ኢሕአፓ በሚያዝያ 1964 ዓ.ም. የተመሰረተ ቢሆንም ራሱን በይፋ ለሕዝብ ያስተዋወቀው በነሐሴ 26/1967 ዓ.ም. ነበር - መርሀ ግብሩን በአማርኛ፥ ኦሮሚፋ፥ ትግሪኛና እንግሊዝኛ ቋንቋዎች በመላ ሀገሪቱ በመበተን፤ ለሀገር ልዕልና፤ ለዴሞክራሲና ለሕዝብ መብቶች ሙሉ በሙሉ መከበር መቆሙን ለኢትዮጵያ ሕዝብ በማብሰር:: የኢትዮጵያ ሕዝብም ከፓርቲው ጎንና ዙሪያ በመሰለፍ ለድርጅቱ ጥንካሬን ሰጥቶታል::

ዛሬ ምስክር ሁሉ የሞተ የተቀበረ እየመሰላቸው የትላንት ፀረ ሕዝቦችና ሽብርተኞች የኢሕአፓን ታሪክ ሊበርዙና ሊያበላሹ ቢቃጡም ኢሕአፓ በኢትዮጵያ ልጆች ለኢትዮጵያ ስርየት የተቋቋመ ሀቀኛ የሕዝብ ድርጅት መሆኑን በደሙ በፃፈው ታሪክ ያረጋገጠውና መቸም ቢሆን የማይፋቅ ሐቅ ነው:: በሰላም መታገል ከተቻለ በሰላም ለመታገል ፍላጎቱን በመርሀ ግብሩ ውስጥ ሳይቀር አስፍሮ ቢገኝም ፋሺስቱ ደርግ ሥልጣንን በእጁ ለማቆየት በሚል አፈናና እመቃን አውጆ በኢሕአፓ ደጋፊዎች ላይ ፍጅትን አደረሰ:: ኢሕአፓ የመጀመሪያዋን የመከላከያ ጥይት ከመተኮሱ በፊት ብዙ የኢሕአፓ አባላት ከአዲስ አበባ እስከ አስበ ተፈሪና አዋሽ፥ ጂማ ተገደሉ:: አንቺ የአዋሽ በረሀ እሪ በይ ምድሪቱ፤ ለኒያ ለባደሮች ለተገደሉቱ የተባለው በዚህ ጊዜ ነበር:: ቀጥሎም ቀይ ሽብር የተባለውም ሰው በላ የግድያ ዘመቻ ታውጆ ከ200 ሺ ያላነሰ ንፁህ ተኪ አልባ ወርቅ ዜጋ ጨፈጨፈ፤ ቀሪውም በጭንቀትና በሀዘን ተናውጦ ህይወቱ ተናጋ::

ኢሕአፓ ራሱን ይፋ ካወጣበት ጊዜ ጀምሮ ፋሺስቱ ደርግ በአንድ በኩል ጠባብ ብሄርተኞችና ገንጣዮች በሌላ በኩል ሆነው ተረባረቡበት:: ሁሉም ብሔረሰብ መገንጠል አለበት ባዩ ወያኔ በተለይ ኢሕአፓን በትምክህተኛነት፤ አማራነትና የትልቋ ኢትዮጵያ ፈላጊነት ፈርጆና በመሰለውም ከሶ ድርጅቱን ለማጥፋት ከ1967 ጀምሮ ተንቀሳቅሷል:: ኢሕአፓ ኢትዮጵያ፤ ኢሕአፓ ዴሞክራሲ ኢሕአፓ አንድነት ማለት ነውናም ፀረ ኢትዮጵያ፤ ፀረ ዴሞክራሲና ፀረ አንድነት የሆኑ የውስጥም የውጭም ጠላቶች አጥቅተውታል:: ኢሕአፓ ግን የሀገርና የሕዝብን ጥቅም ለማንም አሳልፎ አልሰጠም:: ፋሺስቱ ደርግና ጭፍሮቹ ግን አንድ ትውልድን ፈጁ፤ በሀገራችን ታሪክ ታይቶ ያልታወቀ አረመኔ ስየልና ግርፋት በሕዝብ ላይ ፈፀሙ:: ዛሬ ታሪክ በራዦች ጀግኖች ሊሏቸው የተነሱ ሰው በላዎች ጭራቅ መሪን ተከትለው የሰው ሥጋ እየቆረጡ፤ ሕፃናትን ሳይቀር እያሰቃዩ ግፍ የፈፀሙ መሆናቸውን ታሪክ መቸም አይረሳውም:: ኢትዮጵያን ለባዕድ የሸጡ ሀገሪቷን አቁሰለው ለገዳይ ያመቻቹ መንግሥቱና ጭፍሮቹ ሁሌም በታሪክ ተጠያቂ ናቸው::

ነሐሴ 26 በሕዝባችን የትግል ታሪክ ልዩ ምዕራፍን የሚይዘው ይህን ዓይነት አረመኔ ሥርዓት ይወገድ ዘንድ የተደራጀ የሀገሪቷ የመጀመሪያው ዘመናዊ ፖለቲካ ድርጅት ለሕዝብ አለኝታ ለመሆን፤ ለሕዝብ ልሰዋ አለሁ፥ ዝግጁ ነኝ ያለበት የምስራች ቀን በመሆኑ ነው፡፡ እነሆም እስከዛሬ ኢሕአፓ በቃሉ ፀንቶ ለሀገርና ለሕዝብ እየታገለ ነው፡፡ የከፈለው መስዋዕትነት ከባድ ነው፡፡ የደረሰበት ስቃይና መከራም ተፈታታኝ ነበር፤ ዛሬም ነው፡፡ ግን ነሐሴ 26 የዛሬ ሰላሳ አራት ዓመት ሲታወጅ የገባውን ቃል ኪዳን ዛሬም አድሶ ቀጥሏል እንጂ በሀገር አጥፊዎችና ቅጥረኞች ጥቃት አልተሸነፈም፡፡

ኢሕአፓ የኢትዮጵያ ሕዝብ ድርጅት ነው!!
ድል የሕዝብ ነው!!

**EPRP**
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

**EPRP**
BP 22
Bois Colombes 92270
France

**E-mail** ESPIC@aol.com **Website:** http://www.EPRP.com